# ከኢሕአፓ ሌላ ሌላ ኢሕአፓ አለ ወይ?

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሀብቱ ንብረቱ በህይወቱ በአጽሙ በደሙ የመሰረተው የገነባው አንድ ኢሕአፓ ነበር አለ እንደ ሚኖር ያውቃል እንዲኖርም አስፈላጊ መስዋዕትነትን እየከፈለ ይጠብቀዋል እንጂ ማንም እንደ ዳቦ ቆርሶ የሚወስደው አልነበረም አይደለም አይሆንም።በጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ተገዝቶ ቆርሽ እሄዳለሁ ማለት ፉም መዝገን ወይም የቦንብን ጥብቁን ፈቶ በኪስ መያዝ እንደሚሆን የጠና እምነቴ ነው የኢትዮጵያን ንብረት ሰርቆ ለኢትዮጵያ ህዝብ መልሶ ልሸጥልህ ግዛኝ ማለት የማንናቀው ህዝብ ዛሬ በጠላት ተወሮ ቀን ስለቀጠነበት ብቻ መናቅ ለነገው አስከፊ ውርደት ራስን ማዘጋጀት ነው እንጂ ከ ኢሕአፓ ሌላ ሌላ ኢሕአፓ እንዳልነበር እንደማይኖር ግልጽ ነው።ከዚህ በፊት እአአ 1991-92 ዓም ተፈጥሮ የነበረው በከበደ ተሰማ ወይም በሳቱ የተመራው አንጃ ኢሕአፓ እኛ ነን ብለው ሞክረው ነበር ከዛም በወያኔ ርዳታ ኢትዮጵያ ገብቶ እኔነኝ ኢሕአፓ ብሎ ለማወናበድ ሞክሮ ነበር ወያኔም በህልሙ በእውኑም የሚያልመው ኢሕአፓን ማንበርከክ ነው። ለወያኔ ህልም መፍቻ ለመሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ወዶ የተማረከው ኢሕአፓ መሪ ነኝ ብሎ ከበደ ተሰማ ወይም ሳቱ ነው ወያኔም እንዲህያለ ወራዳና ርካሽ የ ኢሕአፓ መሪ ካገኘንማ ሕልማችን ተሣካልን ብለው የኢትዮጵያን ህዝብ የትግል ሞራሉን ይሰብራል ብለው ለሁለት ከሃዲዎች የአይሮፕላን ትኬት ገዝቶ ብስራትና ከበደን ወሰድዋቸው ገና ከዋሽንግተን ዲሲ ሳይነሱ ወያኔ ቴሌቭዥን በሬዲዮና በጋዜጣ የ ኢሕአፓ መሪዎች በቅርቡ ሊመጡ ነው።ብለው አስተዋወቁ በሄዱም ጊዜ ቦሌ አይሮፕላን ማረፊ ደርሰው ከአይሮፕላን ሲወርዱ ብስራትና ጉድ አይፈሬውን ውርደት አይሰለቸውን ከበደን በቴሌቭዥን አሳዩአቸው ብስራትን የሚያቀው ሰው የለም ከበደን ግን ወያኔ ከሚያውቀ በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ግጥም አድርጎ ያውቀዋል ነበር ከዚያ በፊትም ከበረሃ ከድቶ ለደርግ እጁን ሰጥቶ በነበር ጊዜ ተወናብጀ የሚል ጃኬት ደርግ አልብሶ አገሬ ማሪኝ በድየሽአለሁ የሚል ግጥም ጽፎ በሬዲዮ በቴሌቭዥንና በጋዜጣ ስብናውን ሸጦ እውነትን ሸምጦ ክዶ የርኩስ ንዛዜው ተናዞ እንደ ነበር የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቅ ነበር ነገር ግን ወያኔ የ ኢሕአፓ አመራር ናቸው ብሎ ዘፈኑን ያቀልጠው ነበር የስብሰባ አዳራሽ ተዘጋጀ የ ኢሕአፓ አመራሮች ስብሰባ ጠሩ ተብሎ በህዝብ መገናኛ ተነገረ ወያኔ አስገድዶም እንዲሁም በውዴታ አዳራሹ ሞላው እነከበደም ከተደበቁበት በወያኔ አባላት ታጅበው ወደ ኣዳራሹ ገቡ በአንድ የ ኢሕአፓ አባል ነበር ከሀዲ እንኳ ደህና መጣችሁና የማስተዋወቂያ አጭር ንግግር አደረገና ከበደን እንዲናገር ጋበዘው ከበደም ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ፖዴሙ ሲሄድ ከፖዴሙ ሳይደርስ እንክርዳድ እንደ በላች ፍየል ወይም በስተት ኮኬን እንደ ቃመች ዥንጀሮ አእምሮውን ስቶ አጓጉሮ ወደቀ ወያኔም ሩጦ የአዳራሹን መብራት አጠፋ ስብሰባውም መብራት ጠፋ በሚል ተበተነ ከበደ ለወያኔ ትርፍ ሳይሆን ኪሳራ ሁኖ ተባረረ ከበደ ወደ ኢሕአፓ እንዴት ተመልሶ ገባ የሚል ጥያቄ ተነስቶ ብዙ ውዝግቦችና መካረሮች ተነሥተው ነበር ተመልሸ ወዳለፉት ንትርኮች ለመግባት አይደለም ከከበደ ተመልሶ ወደ ኢሕአፓ መግባትና ከበደ መልሶሞ ኢሕአፓን መካድ ምንነቱ የማይታወቀው ዘሪሁን ተሾመ ወደ ኢሕአፓ መግባት ዘሪሁን ተመልሶ ኢሕአፓን መካድ እንዲሁም በፓርቲውና በሠራዊቱ ላይ ከፍተኛ ወንጀል ሰርተው የሄዱትን ግለሰቦች ጸሀየ ሰለሞን ገብረስላሴ ደሳለኝ ወይም ዶክተር ዜሮ ወደ ድርጅቱ ተመልሰው ገብተው ከፍተኛ የአመራር ቦታ ይዘው ቆይተው እንደገና የክደት በሽታቸው አገርሽቶባቸው እንዲሁም ሌሎችን እውር ውሻዎችን ጨመረውና ኢሕአፓም ትግሉንም ከደው እንዲሁም ነባርና ጠንካራ የድርጀቱን አባላት ወንጅለው የአደሩበትን የሆቴልና የበሉትን የጠጡተን ሂሳብ ሳይከፈሉ በለሊት ከድተው ሂደው ኢሕአፓዴ መስርተና አሉ ለምን ኢሕአፓ እኛ ነን አላሉም ምክኒያቱም ኢሕአፓ ኢሕአፓ ነው ተጎታች ሆነ ተሳቢ ወይም ተለጣፊም የለውም ኢተዮጵያም አንድናት ኢሕአፓም አንድ ነው ከ ኢሕአፓ ሌላ ሌላ ኢሕአፓ ሊኖር አይችልም።ከበደ ኢሕአፓ እኔ ብሎ ስሙን ይዞ ሲሄድ ዮወሴፍ መርሻ ወይም መርሻ ዮወሴፍ የተናገረው ጥሩ ነገር ነበር። ከበደ መታገል ከከበደው መሄድ ይችላል ግን ኢሕአፓ የናቱ ዘንቢል አይደለም አንጠልጥሎት የሚሄደው ብሎ ነበር። ከ24 ዓመት በኋላ ዮወሴፍ መርሻ የኮባ ቅጠል ሁኖ አገኘው እንዴ አንጠልጥሎት የሄደው። ያም ሆነ ይህ ከ ኢሕአፓ ውስጥ የነበረው የነቀርሳ ሴል ወይም ነቀርሳው ከስሩ ተሞንቅሎ የወጣ መሆኑን የሚያሳዩ ሁኔታወች ተከስተዋል። አንጃውና ባንዳው እንዲሁም አንዳንድ የተምታታባቸው ግለሰቦች ለምሳሌ እንደ ቃሲም አይነቱ በጸረ ወያኔና በአገር አድኑ ትግል ላይ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቀው ግለሰብ ጭምር ከየትም ተጠረቃቅመው ኢሕአፓ አንድነት በሚል ስም በባሊቲሞር ሜሪላንድ እውነተኛውን ኢሕአፓ ለመታገል ከተሳካም ለማፍረስ ከጁን 28 ቀን እስከ ጁላይ 1 ቀን 2015ዓም ጉባኤ አደረግን በለዋል። መግለጫም ጉባኤው በሚያስደስት ሁኔታ ተጠቃለለ ብለው አውተዋል። ከዚያም የርማት እንቅስቃሴ የሚለው ቡድንና ኢሕአፓዴ አንድ ለመሆን ተፈራረምን ብለዋል። ነገሩ ዋው የሚያሰኝ ነው። ይች ጡረታ የወጣች አራዳነት ናት ቂላችሁን ፈልጉ ከመጀመሪያውስ መቸ ተለያችሁ። ጀሮ እንዲጠቡ አስቀምጣችኋቸው ከሄዳችሁት ጀሮ ጠቢ ጋር ግንባር ፈጠራችሁ። በድጋሜ ዋው ዋው የሚያሰኝ ነው።ከአንደኛው መሪያቸው ከዶክተር ዜሮ አንድ የእንግሊዘኛ ጥቅስ ልውሰድ። ዶክተር ዜሮ ወይም ደሳለኝ ከአንድ ወገን ጋር በጽሁፍ ክርክር ገጥሞ የሚከራከርበት ነጥብ ሲያንሰውና ሲጠፋው እንደ አለው ``I found the heap lies and your garbage on AIGA FORUM=YOU belong there, I am very happy for you to have found your final address. Congratulations``.ተሰበሰበ የተባለው ሁሉ የደም እረጋኝ የከሀዲ ጥርቅም ትግሉ አሽቀንጥሎ የጣለው የሰው ቆሻሻ (Garbage)ነው። ለ ኢሕአፓ አንድነት ሳይሆን ትግሉና ኢሕአፓን ለማዳከም ነው። ኢሕአፓን ለማፍረሥ ሕይወቱ በሞላ የታገለ፣ ሠራዊቱ ያፈረሠ፣ የድርጅቱን ሚስጥር ለጠላት አሳልፎ የሰጠ፣ በአየጋ ፎረም ሰብሳቢነት ተሰብስቦ ለ ኢሕአፓ አንድነት ብሎ ለማታለል መሞከር፣ ትዝብት ነው ሺ ባንዳ ከአንድ ላይ ቢጨፈለቅ አንድ ጀግና አይወጣውም። ሺ ውሸት ከአንድ ቢጨመቅ የእውነት አንዲት ጠብታ አይወጣውምና ሌላው ሳይሆን እራሳችሁን ነው ያታላችሁ፣ ያሞኘታችሁ። በመውጣታችሁ ምንም አሁን ኢሕአፓ አባል ባልሆንም በቀድሞ አባልነቴና በአሁን የ ኢሕአፓ ደጋፊነቴ በጣም ነው የተደሰትሁት። ከእንግዲ በኋላ የ ኢሕአፓን ስም ኢሕአፓን አርማ መጠቀም አይቻለም። የ ኢሕአፓ አመራርና አባላት ኢሕአፓ ስም አርማ ማንም እንዳይጠቀመበት የመጠበቅ የማስከበር ድርጅታዊ፣ ህግአዊና ሞራላዊ አላፋነት አለበት።ከ ኢሕአፓ ሌላ ሌላ ኢሕአፓ አልነበርም፣ አይኖረምም። ሌላ ኢሕአፓ ነኝ ብለው ሁለት እንደ ሚከተለው ሰተዋል

፪-P.O. BOX 88675. LOS ANGELES, CA 90009

በ ኢሕአፓ ሥም ገንዝብ ለመሰብሰብ አድራሻዎች ሰጠዋል። በማን ስም እንደ ተመዘገቡ ፈልጎ ያስመገበው ግለሰብ ሆነ ግለሰቦች በማንነት ስርቆት (Identity theft protection LAW)መክሰስና የሰበሰቡትን ገንዘብ ማስመለስ አድራሻዎችንም ማዘጋትና ድግም ኢሕአፓን ሰም አርማውን እንዳ ይጠቀሙ የማድረግ የእውነተኛ  ኢሕአፓ አመራርና አባላት ግዴታ አለበት። ከ ኢሕአፓ ሌላ ሌላ  ኢሕአፓ አልነበርም። የለምም። ለወዲፊቱ አይኖርም። ይህን የማያምን የ ኢሕአፓ አባል ካለ ከድርጅተ መባረር አለበት። በአሁኑ ጊዜ የሚያስፈልገው ከብዛት ጥራት ነው። ከጥራት ጥንካሬ፣ ከጥንካሬ ብዛት፣ ይመጣልና ማንም ወዶ ተማራኪ ማንም አውደልዳይ አድርባይ አጠረቃቅሞ ትግል እታገላሁ ማለት ትግሉን መጉዳተና ጠንካራ አባላትን ማሰቃየትና መጉዳት ነው።ዘንድሮ በማያሻማ ሁኔታ ታጋዩ ከባንዳው፣ ከደም እረጋጩ፣ አንጃውና ከአድርባዩ ጋር ጥራት ባለ ሁኔታ ተለይቷል። ይኼ ልዩነት መጠንከር መጎልበት አለበት። ምክንያቱም ውሃን ማላመጥ ጠላትን ወዳጅ ለማረግ መሞከር አጉል ልፋት ነው። ለምሳሌ ለ30 ዓመታታ ቀድሞ የ ኢሕአፓ አባል የነበሩና ቀጣይ  ኢሕአፓ አባል የሆኑ አመታዊ ምሽት እየተባለ ሲከበር የነበረው ከሁለት ተከፍሎ ተከበረ። በአንዳኛው አንጃውና የወያኔው ጀሮ ጠቢዎች ተሰባስበው በአንድ ምግብ ቤት ሲያከብር እንዲሁም በርካታ የ ኢሕአፓ አባላትና የ ኢሕአፓ ደጋፊዎች በ ኢሕአፓ አርማና በኢትዮጵያ ሰደቅ ዓላማ ባሸበረቀ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ አከበሩ በሌላ በኩልም መህል ሰፋሪውና አድርባዩ ከሁላችሁም አንደርስም ብሎ ወደ የመጡበት ተመልሶ ሄደ።

ከዚህ በኋላ ግልጽ እንዲሆን የሚያሰፈልገው በዓመት አንድ ቀን መጋናኛችን መሰባሰቢያችን እንዳይፈርስ ከተከራከሩት ከታገሉት አንዱነኝ። በተለያዩ ጽሁፎቸ ውስጥ አማራው ተጠንቀቅ አያድርስ አሸከርነት በእርጅና ደም ጓጉሎ ቢቀመጥ የአፈር ክምር አይደለም (በኢትዮጵያ ረጅስተርና ሐዋሪያ)እንዳይነካ ጠይቀአለሁ። እየተነካ መሆኑን ጠቁሜ ነበር ግን ሰሚ ጠፋ ችግሩን መፍቻ ዜዴ ጠፍቶ ከተንኮል ላይ ተንኮል ተደራርቦ ስለመጣ የአለው አማራጭ ሲመሰረት የተስማማንበት ለአንድ ቀን ሁሉን ነገር ይቅር ብለን ለትላትናው ስንል ተቻችለን በዓመት አንድ ቀን መጋናኘት በሚለው መሠረት ግኑኝታች በትናትና ነውና ጓዶችን ገድሎ የሄደው የድርጅቱ ሚስጢ ለጠላት አሳልፎ የሰጠው፤የድርጅቱን ንብረት ሰርቆ የሄደው ሰራዊቱን በትኖ የሄደው ሲታገልበት የነበረውን መሳሪያ ሽጦ የበላው የተቀብረ መሳሪያ ለሱዳን መንግስት ጠቁሞ ያስወሰደ ሁሉ፤እንዲሁም ከተማ አባል ነበር ነበረች እየተባለ የመኢሦንና የኢሠፓ፤ነፍሠ ገዳዮች ሁሉ፥እየመጡ ተዝናንተው ተገብዝው ይሄዱ ነበር። የማናውቀውን ጠላት እየጠሩ ማምጣቱ አልበቃ ብሎ የምናውቀን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያን ህዝብን ጠላትና በርካታ የእኛን ጓዶች ያረድውን የገደለውን ፋሽስቱ አረጋዋ በርሄን ተጋብዞ የጣመ ችግር ተፈጠረ አስወጡ ተባለ። በልቶ ጠጥቶ ሄደ። እንዲሁም ወያኔ የዛን ትውልድ ታሪክ ለማጥፋት የጀሮ ጠቢዎቹን ስም ተጠቅሞ የፃፈውን መጽሐፍ እንዲሸጡ መፍቀድ ትናንትናን ለማዋረድ ነው መጽሐፍ ፃፈው የመጡት የተባሉት እንኳ 7መቶ 8መቶ ገጽ አለው በአማረኛ መጽሐፍ ይቅርና አማረኛ በትክክል የማይናገሩ የማይገባቸ ናቸው። እነዚህን ማንበብ መፃፍ የማይችሉ የትግሬ ምሁራን!! የጻፉትን መጽሐፍ ይሺጡ ብሎ መፍቀድ ወራዳነት ተደፊነት ነው። እንዲሁም አረጋዊ በርሄ በየትኛው ቦታና ጊዜ  ኢሕአፓ ጠላት እንጂ የ ኢሕአፓ አባል አልነበብረም አይሆንንም።

በትናትናው ስህተት ዛሬ መጸጸቱና በተመዘገበው ጀግንነት ዛሬ መደሰቱ የነበረ ያለ የሚኖር ለሰው ልጅ ተፈጥሮ የሰጠችው የጋራ ስጦታ ነው።የተፈጥሮ ህግጋት የማይረዱ ከ ኢሕአፓ ውስጥ የወጡት አንጃዎችና ባንዳዎች ስህተቱን ወንጀሉን እነሱ መስራተቸውን ክደው ለተገኘው ድል ወራሽ ሁነው የተሰራውን ስህተት አሁን ለአሉ የ ኢሕአፓ አመራርና አባላት ላይ ይዳርጋሉ። ነገሩ ይገርማል የ ኢሕአፓን አመራር አባላት ዲክታተር ብሎ የወያኔን አመራር ዴሞክራት ነው ማለት ሂሳዊ ድጋፍ ካለው መኢሶን በላይ በደም የከረፋው በዮሴፍ መርሻ የሚመራው ደም እረጋጭ አንጃ ነው። ይሄ ትናት አብረን ነብርን ለሚለው አወ እኛ አብረናቸው ነበርን፤ እነሱ ግን ከእኛ ጋር የነበሩት ተቀጥረው ለተቀጠሩበት አላማ እንጂ ከኢትዮጵያ ህዝብ ትግል አኳያ እንዳልነበር የትናት ስራቸውና ዛሬ የሚሰሩት ሥራ ታላቅ ታሪካዊ ሰነድ ቃለ ጉባኤና ታላቁ ሴራ በ ኢሕአፓ ሲጋለጥ ነውና ከእንዲህ በኋላ ጉዞ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አይሆንምና ምርጫችንን እናስተካክል።

አቸናፊ አራጋው
ንሀሴ 2007 ዓም     august 2015